"

# ልዩነት የግድ ካለ በልዩነታችን ውስጥ ያለውን አንድነት እንመልከት።

"የተመቻቸ ነገር አለመኖሩ እንጂ ግንቦት7 ከአንድነት የሚቀርበው ድርጅት የለም"አንዳርጋቸው ጽጌ

በጌታሁን አባተ

በግንቦት 97 ዋዜማ የተመሰረተውና በወያኔ አገዛዝ ላይ ታሪካዊውን ድል የተጎናጸፈው ቅንጅት የተንቀሳቀሰው በግዜው ልዩነቶቻቸውን አቻችለው አንድ በሚያደርጓቸው ጉዳዮች ላይ ለመስራት በተስማሙ የተቃዋሚ ድርጅቶች ህብረት ነበር። በአንድነትም ውስጥ ልዩነት ነበርና ልዩነታቸው ጎልቶ (የግለሰቦች ባህሪ የጠነሰሰው ቢሆንም) እንሆ ዛሬ ለምንገኝበት ደረጃ በቅተናል። በአንድነት ውስጥ ልዩነትን አቻችሎ መጓዝ አልተቻለም። መለያየት ግድ አለ። ይሁንና በልዩነትም ውስጥ አንድነት አለና ዛሬ ደግሞ በልዩነታችን ውስጥ አንድነታችንን አቻችለን መሄድ ግዜው ግድ የሚለን አማራጭ የሌለው የጉዞ መስመር ነው።

ይህን ሃሳብ ለዚህ ጽሁፌ መንደርደሪያ አድርጌ ያነሳሁት በትናቶቹ ቅንጅቶች በዛሬዎቹ የአንድነት ፓርቲና ግንቦት7 ንቅናቄ መካከል እየታየ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመመለካከት ፈልጌ ነው። ለዚህ ጽሁፌም አብይ ምክንያት የሆነኝ በቅርቡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በከረንት አፌርስ የውይይት መድረክ (ፓልቶክ) ተገኝተው ያደረጉት ለሁለት ሰአታት ጥቂት ደቂቃ ጉዳይ የዘለቀ ቃለ መጠይቅ ነው። ይህን ቃለ መጠይቅ ያላደመጠም ካለ ይህን ጽሁፍ ማንበቡን አቁሞ እንዲያደምጥ ምክሬ ነው። መደመጥ ብቻም ሳይሆን መላመጥ ያለበት ቃለ መጠይቅ ነውና።http://www.ecadforum.com/files/ginbot7_16_11.ram

ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ስመለስ በቅድሚያ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ባደረጉት ቃለ ምልልስ እጅግ በጣም የረካሁ መሆኔን መግለጽ እወዳለሁ። እርካታህ ከምን አንጻር ከተባልኩም፡- አዎ በቃለ መጠይቁ የረካሁት ብዥታዎችን ያጠራ ልዩነት አስፈ ሽብልቆችን የነቀለ ባጠቃላይ የግንቦት7 ንቅናቄን አቋም ለሚደግፈውም ለሚነቅፈውም እኩል ግልጽ ያደረገ ስለነበር ነው። አንድን የፖለቲካ ድርጅት ለመደገፍም ይሁን ለመንቀፍ የድርጅቱን አቋም በጥንቃቄ መረዳትን ይጠይቃልና።

በተለይ የተለያየ የትግል ስልት የሚከተሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች (ግባቸው አንድ ቢሆንም) በተከሰቱበት በወቅቱ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ጥንቃቄን የሚጠይቁና እርስ በእርስ ከመጠላለፍ በጸዳ መልክ መከወን እንደሚገባቸው የበለጠ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ምክንያቱም በተቃዋሚ ድርጅቶቹ መካከል ያለው የትግል ስልት ልዩነት በራሱ በርካታ ውስብስብ ልዩነቶችን እየፈጠረ ለደጋፊዎችም ሆነ ለድርጅቶቹ መሪዎች እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁነቶችን ሲፈጥር እያታዘብን ነውና።

ለአብነት ያህል ማንሳት የምሻው በግንቦት7 ንቅናቄና በአንድነት ፓርቲ መካከል ያለውን የትግል ስልት ልዩነት ሲሆን፡- የድርጅቶቹ መሪዎች ድርጅታቸው ስለመረጠው የትግል ስልት በሚያስረዱበት አጋጣሚ ሆን ብለውም ባይሆንም የሌላኛውን ተቃዋሚ አካሄድ አያዋጣም አይነት

ትርጉም ሊሰጠው የሚችል መግለጫ ሊሰጡ የመቻላቸው ዕድል በጣም የሰፋ በመሆኑ የሁለቱም ወገኖች እንቅስቃሴ በመቻቻልና በጥንቃቄ ሊከውን እንደሚገባ እየተረዳን ያለነበት ወቅት ነው ያልኩትም ለዚህ ነው።

አቶ አንዳርጋቸው በቃለ መጠይቃቸው ያስረዱን፡-ድርጅታቸው ያዋጣኛል ብሎ ስለመረጠው የትግል ስልት እንጂ አያዋጣም ብሎ ስለሚያምንበት የትግል ስልት አልነበረም። መሆንም ያለበት ይህ ነው። ግንቦት7 ንቅናቄ ምንም እንኳ አመጽን ያማከለ ሁለ ገብ የትግል ስልትን የመረጠው ወያኔ በከለለው የሠላማዊ ትግል አጥር ውስጥ ሆኖ የሚደረግ ትግል የትም አያደርስም (ሰላማዊ ትግል አያዋጣም) ከሚል ግምጋሜ በመነሳት ቢሆንም እንደ አቋም የሚጠቅሰው ግን ያዋጣል ያለውን ስልት እንጂ አያዋጣም ስለሚለው ሥልት አይደለም፡፤

የሁለቱም ድርጅቶች መነካካት በዚህ ነጥብ ዙሪያ ይመስለኛል። አንድነት ፓርቲም እንደ አቋም እንዲያንጸባርቅ የሚጠበቀውም ሠላማዊ ትግል ብቸኛው የትግል ስልት መሆኑን እንጂ አመጽና ኃይልን ያማከለ ስልት አያዋጣም የሚል አይሆንም። በርግጥ ጥንቃቄና መቻቻል ካልታከለበት በስተቀር እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን የትግል ስልት ትክክለኛነት ለማስረዳት በሚንዝበት ጎዳና የሌላውን ድርጅት ስልት መቧጠጡ ሙሉ ለሙሉ ሊወገድ የሚችል አይሆንም። ምክንያቱም አምክኖታዊ ትንተናዎች የተቃራኒን ወገን ሃሳብ ኢ-አምክኖታዊነት ከማስጨበጥም ሊነሱ የመቻላቸውን ዕውነት ለመቀነስ እንጂ ለመገደብ አይቻልምና ነው።

ይሁንና መታሰብ ያለበት ውናው ቁም ነገር (አቶ አንዳርጋቸውም አስረግጠው እንደገለጹት) ግንቦት7 የሚያዋጣው አመጽንና ሃይልን ያማከለ የትግል ስልት ነው ሲል አንድነት ለመቃወም ሳይሆን ወያኔን ለመጣል ይበጃል ብሎ የወሰደው አቋም እንደሆነ ተደርጎ ነው። በተመሳሳይ መልክ አንድነትም ሠላማዊ የትግል ስልት ብቸኛውና አማራጭ የሌለው የትግል ስልት ነው ሲል፤- ወያኔ ሊወድቅ የሚችለው በዚህ ስልት ብቻ ነው ብሎ በማመኑ እንጂ የግንቦት7ን አካሄድ መቃወሙ እንዳልሆነ ነው።

የትግል ስልታችንን የነደፍነው ከወያኔ ባህሪ ተነስተን እንጂ ከአንድነት ወይም ከሌላው ተቃዋሚ ድርጅት አቋም ተነስተን አይደለም ሲሉ አቶ አንዳርጋቸው የገለጹትም ይህንኑ ይመስለኛል።

ምንም እንኳ የትግል ስልታቸው ቢለያይም በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት የሁለቱ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ወያኔን ከግራና ከቀኝ ወጥሮ የሚይዝ ተደጋጋፊ የትግል እንቅስቃሴ ነው፡፤ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት ግንቦት7ንም ሆነ አንድነትን ለማጣጣል የሚነሳን አካል አብዛኛው ኢትዮ ጵያዊ የሚቃወመው። ለዚህም ነው በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ተጠላላፊ ጉዳዮች ሲነሱ በሰከነ መልክ ለማርገብ የሚሞከረው።

ለምሳሌ የኢትዮጵያን ሪቪው አዘጋጅ (መንገድም ህይወትም ሻቢያ ነው) ባዩ ኤልያስ ክፍሌ ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ ተንተርሶ አንድነት ፓርቲን ለመስደብና ለማንኳጠጥ ባደረገው ሙከራ አይንህ ላፈር መባሉ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው። ዛሬ በአንድነትና በግንቦት7 መካከል እሳት ፈጥረው ዋናውን ጠላት ወያኔን እንድንረሳና እርስ በእርስ እንድንራኮት የሚሹት እንደ ኤልያስ ያሉ ድብቅ የግል አላማ ያላቸው አልያም እራሳቸው ወያኔዎች ብቻ ናቸው።

አቶ አንዳርጋቸው በቃለ መጠይቁ ከተናገሩት ውስጥ ሌላው የያዝኩላቸው ትልቅ ነጥብ። "የተመቻቸ ነገር አለመሆኑ እንጂ ለግንቦት7 ከአንድነት የቀረበ ድርጅት የለም ያሉት ነው፡፤ የተመቻቸ ነገር ሲመጣ ማለትም በሃይልም ይሁን በሠላማዊ ትግል ወያኔ ከተወገደ በኋላ በሚከተለው የዲሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ አንድነት ና ግንቦት7 አንድ አይነት እምነትና ፍላጎት እንደሚኖራቸው ያላቸውን እምነት ሲገልጹ ነው። የትግል ስልት ልዩነት ዋናውን የዓላማ አንድነት አያናጋም የምንለውም ለዚህ ነው።በልዩነት ውስጥ አንድነት አለ የምነለውም ይህንኑ ነው።

እንዳፋቸው ያድርገልንና አቶ አንዳርጋቸው የአሁኑን ዝምታ "ከማዕበሉ በፊት ያለ ዝምታ" አድርጋችሁ ውሰዱት በማለት ማዕበሉ በቅርብ እንደሚጀምር እርግጠኝነት በተሞላበት መንፈስ ተናግረዋል። ከዚህ የተረዳሁት ሥራ መሠራቱንና እየተሠራም መሆኑን ነው።ይበል ይቀጥል ያሰኛል።

ሌላው አቶ አንዳርጋቸው ግልጽ አድርገው ያለፉት በአመጽ ትግሉ መሳሪያ ትጠቀማላችሁ ወይ የሚለውን ከግንቦት7 ምስረታ ጀምሮ ሲንከባለል የቆየውን ጥያቄ ነው። አይደለም መሣሪያ አስፈላጊ ከሆነ ከዚያም የበለጠ ነገር እንጠቀማለን ነበር ያሉት። ሲንከባለል የቆየውን ጥያቄ ታኮ አስገብተው አቆሙት። በኔ እምነት ከዚህ በኋላ ይህ ጥያቄ አይነሳም። ትንታኔና ማብራሪያ የሚያሻው ነገር ብዙም አይታየኝም።

አሁንም በኔ እምነት አስፈላጊ ነው የምለው የአንድነትም ሆነ የግንቦት7 መሪዎች በሚሰጡት መግለጫ የትግል ስልታቸው ልዩነት ግድ ብሎ ተነቃቃፊ ሃሳቦችን ቢሰነዝሩ እንኳ ሃሳቦቹ ያነጣጠሩት በዋናው ጠላት በወያኔ ላይ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ተቻችሎ መስራት እንዳለባቸው ማመናቸውን ነው። እኛም እንደ እምነታችን ለፈለግነው ድርጅት ድጋፍ የመስጠት መብታችን የተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ግንቦት7 ንቅናቄን ለመደገፍ አንድነትን መቃወም ሳያስፈልገን አልያም አንድነትን ለመደገፍ ግንቦት7ን መቃወም ግድ ሳይለን በተጠናና በሰከነ የልዩነት አንድነት ጎዳና ልንጓዝ ይገባናል እላለሁ።

ጋዜጠኞችም ቢሆኑ የሁለቱን ድርጅቶች መሪዎች በሚጠይቁበት ወቅት አንዱን ከአንዱ አወዳዳሪ የሆኑ ጥያቄዎችን ማስወገድ ይገባቸዋል። ይህ አይነቱ አካሄድ ወደ አላስፈላጊ ውዝግብ እንደሚያመራ ከኤልያስ ክፍሌ መረን የወጣ ሥራ የተገንዘብን ይመስለኛል።

ዋናውን አደራ ላቀብል የምሻው ግን አሁንም ለድርጅቶቹ መሪዎች ነው፡፤

የአንድነት መሪዎች የድርጅታቸውን አላማና አካሄድ በሚያስረዱበት  ወቅት የግንቦት7 መሪዎችን መግለጫ ወይም ንግግር ኢ-ምክንያታዊነት በማስረዳት ወይም በመግለጽ መሆን የለበትም እላለሁ። የግንቦት7 መሪዎችም አመጽ ብቻ ትክክለኛው የትግል ስልት መሆኑን ለማስረዳት የወ/ሮ ብርትኳንን መግለጫ ማብጠልጠል ወይም ስህተትነት መተንተን የለባቸውም። ይህ ሲሆን ብቻ ነው በልዩነታችን ውስጥ ያለውን አንድነት ማየት የምንችለው።
የኢትዮጵያ አምላክ ሁላችንንም ይርዳ!!!